በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF FOREIGN AFFAIRS
የፕሬስ መግለጫ
PRESS RELEASE

# ኢትዮጵያ ድህነትን ለመዋጋት እየሰራች ነው




ኢትዮጵያ ባለፉት ተከታታይ ዓመታት ያስመዘገበችው የኢኮኖሚና ማህበራዊ ዕድገት በርካታ ህዝቦቿን ከድህነት ወለል በታች ያስወጣ መሆኑ ተገለጸ፡፡

ዶ/ር ይናገር ደሴ የብሄራዊ ፕላኒንግ ኮሚሽን ሚኒስትር ኒውዮርክ በተካሄደው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የኢኮኖሚና ማህበራዊ ጉዳይ ምክር ቤት ስብሰባ ላይ ባደረጉት ንግግር ከ15 ዓመት በፊት 44 በመቶ የሚሆኑ ህዝቦቿ ከድህነት ወለል በታች እንደነበሩና ይህ አሀዝ ወደ 22 በመቶ ዝቅ ማለቱን ገልጸዋል፡፡

ይህ አሀዝ በቀጣይ ሁለት ዓመት ወደ 17 በመቶ ያህል ይወርዳል ተብሎ የሚገመት ሲሆን መንግስት ለዚህ ዘርፈ ብዙ ተግባራትን እያከናወነ መሆኑን ዶ/ር ይናገር ጠቅሰዋል፡፡

ዶ/ር ይናገር በኒውዮርክ በተካሄደው የኢኮኖሚና ማህበራዊ ጉዳይ ምክር ቤት ዓመታዊ መድረክ ላይ ተገኝተው የአገራችን የዘላቂ ልማት አተገባበር ሪፖርት ባቀረቡበት ወቅት እንዳሉት መንግስት ድህነትን ለማስወገድ የላቀ ሚና ባላቸው የትምህርት፣ የጤና፣ የግብርናና ተያያዥ ዘርፎች ከፍተኛ በጀትና የሰው ሃይል በመመደብ እየሰራ ነው፡፡አገሮች ድህነትን ለማስወገድ በሚያደርጉት ጥረት ዓለም አቀፍ ትብብር አስፈላጊ በመሆኑ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ዶ/ር ይናገር ደሴ ጠሪ አቅርበዋል፡፡

**የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ ጽ/ቤት**

**ሃምሌ 15 ቀን 2009 ዓ.ም**

P.O.BOX 393 TEL: 011 5 517345 FAX: 011 5 514300 E-mail: mfa.press@ethionet.et Website: www.mfa.gov.et